በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር 4.0/16/10
Ref. No
ቀን 04 መጋቢት 2010
Date

የጉምሩክ ሥነ-ስርዓት ለሚፈጸምባቸዉ ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ"ን በመጠቀም የሚገጣጥሙ አምራቾችን ይመለከታል</u>

የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ"ን በመጠቀም የሚገጣጥሙ አምራቾች የሚያስመጧቸዉ ግብዓቶች ላይ የጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ" አጠቃቀም ላይ እያጋጠመ ያለዉን ክፍተት በመዘርዘር አስፈላጊዉ ጥንቃቄ እየተደረገ አገልግሎቱ እንዲሰጥ ከዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት በቁጥር 3.1.0/470/10 በ14 ጥር 2010 በተጻፈ ደብዳቤ መተላለፉ ይታወሳል፡፡ ሆኖም በእንጥልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮች እና ለወደፊቱም በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገቡ ለመገጣጠሚያ ፋብሪካዎች የሚሆኑ ግብዓቶች የሚስተናገዱበት አግባብ ከሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት ማብራሪያ እስከሚሰጥ ድረስ ግልጽ አቅጣጫ አልተሰጠም፡፡ ስለዚህ በ22/06/2010 ዓ.ም. የባለድርሻ አካላት ማለትም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ከብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና የሚመለከታቸዉ የጉምሩክ ዘርፍ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎችና ሠራተኞች በተገኙበት በእንጥልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮችና ለወደፊቱ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚገቡ ለመገጣጠሚያ ፋብሪካዎች የሚሆኑ ግብአቶች የሚስተናገዱበትን አግባብ መመሪያ ቁጥር 45/2008ን እንደተሻሻለዉ መሰረት በማድረግ የጋራ መግባባትና ዉሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡

በመሆኑም፡-

1. በአገር ዉስጥ ለመገጣጠም ተብለዉ የሚገቡ ነገር ግን በሀርሞናይዝድ ሲስተም የአተረጓጎም ደንብ ቁጥር 1 እና 2(ሀ)ን መሰረት በማድረግ ሲታዩ እንደተጠናቀቀ እቃ ተቆጥረዉ የተጠናቀቀዉ እቃ ሊመደብበት በሚችለዉ የታሪፍ ቁጥር ላይ የሚመደቡ ከሆነና ይሄዉ የተጠናቀቀዉ እቃ በሁለተኛ መደብ በአገር ዉስጥ ለመገጣጠም ሲመጣ ወይም እንደገና ለመሠራት ሲመጣ ተብሎ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ያልተካተተ ከሆነ ምንም እንኳን በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል የጉምሩክ ታሪፍ የሁለተኛ መደብ "ሀ" ተጠቃሚነት ሰርተፊኬት የተሰጠ ቢሆንም እንደማንኛዉም የተጠናቀቀ የንግድ እቃ ተቆጥሮ በጉምሩክ ታሪፍ አንደኛ መደብ መሰረት ቀረጥና ታክሱ እንዲሰበሰብ በጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች በኩል አስፈላጊዉ እንዲፈጸም ተወስኗል፡፡
2. በአገር ዉስጥ ለመገጣጠም የሚገቡ ነገር ግን በአንደኛ መደብ የተጠናቀቀዉ እቃ የሚመደብበት የታሪፍ ቁጥር ተጠቅሶ በጉምሩክ ታሪፍ የሁለተኛ መደብ "ሀ" እንደገና ለመሥራት ወይም በአገር ዉስጥ በታወቀ ፋብሪካ ለመገጣጠም ከሚገቡት እቃዎች ዉስጥ የቴሌቪዥን ገጣጣሚዎች የሚያስገቡት ቴሌቪዥን በሀርሞናይዝድ ሲስተም የታሪፍ አተረጓጎም ደንብ ቁጥር

1 እና 2(ሀ) መሰረት የተጠናቀቀዉ ቴሌቪዥን የሚመደብበት ታሪፍ ቁጥር ላይ የሚመደብ እቃ ስለሆነ በሁለተኛ መደብ የተፈቀደዉ ቴሌቭዥን (በአገር ዉስጥ ለመገጣጠም የመጣ ቴሌቭዥን) ይህንኑ የታሪፍ አተረጓጎም የሚያሟላ መሆኑ እየተረጋገጠ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ" የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በሚሰጠዉ የተጠቃሚነት ሰርትፍኬት መሰረት እንዲስተናገድ ተወስኗል፡፡ ነገር ግን በዚህ ሁኔታ በአገር ዉስጥ ለመገጣጠም የሚገባዉ ቴሌቭዥን በምን ያህል ደረጃ ሳይገጣጠም ሲመጣ የመብቱ ተጠቃሚ መሆን እንዳለበት ማብራሪያ የሚያስፈልገዉ በመሆኑ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል ግልጽ ትርጉም እስከሚሰጥበት ድረስ የአምራች ደርጅቶች ከሚያቀርቡት ከፍተኛ ቅሬታ አንፃር የእቃዉ ናሙና ቀሪ እየተደረገ የመብቱ ተጠቃሚዎች በቀጠይ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት ለመስተናገድ የደብዳቤ የዋስትና እያቀረቡና የዲ/ዮን ሰነዶች ሳይበተኑ እንዲስተናገዱ ተወስኗል፡፡

3. ሌሎች በአገር ዉስጥ ለመገጣጠም የሚገቡ እቃዎች በሀርሞናይዝድ ሲስተም የታሪፍ አመዳዳብ አሠራር እና የአተረጓጎም ደንቦች መሰረት የታሪፍ አመዳዳባቸዉ ሲወሰን በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ" የሚካተቱ መሆናቸዉ ሲረጋገጥ በመመሪያ ቁጥር 45/2008 እንደተሻሻለዉ እና በባለስልጣኑ መመሪያ ቁጥር 126/2009 መሰረት አስፈላጊ የሆኑት ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያሟሉ መሆናቸዉን በማረጋገጥ መስተናገድ አለባቸዉ፡፡
4. በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ለሚስተናገዱ አምራቾች በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በኩል የተጠቃሚነት ሰርትፍኬት ሲሰጥ እና ይህንኑ መሠረት በማድረግ በጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በኩል የጉምሩክ ስነ-ስርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ በእቃዎቹ የታሪፍ አመዳደብ ላይ ሙያዊ እገዛ ወይም ማብራሪያ ካስፈለገ በመመሪያዉ መሰረት የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬትን መጠየቅ ይችላል፡፡
5. ከዚህ ጋር በተያያዘ በእንጥልጥል ላይ ያሉ ውሳኔ የሚጠብቁ ጉዳዮች ከላይ በተቀመጠዉ አቅጣጫ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጌቱ ለገሠ
የጉምሩክ ዘርፍ ተወካይ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Revenues & Customs Authority

ግልባጭ፡-
- ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
- ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
  አዲስ አበባ
- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሕግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለአምራች ወጪ ንግድ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
  ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን